ኢትዮሚዲያ

ርእሰ አንቀፅ

# ያብለጨለጨ ሁሉ ወርቅ ነው።

ትርጉም ጠጂቱ ዲባባ

" ያ የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ አይደለም" በብዙ ሚሊዮን ዶላር በሚቆጠር ወርቅ የሚገዙና በሳጥን የሚያጠራቅሙትን የኢትዮጵያ የባንክ ባለሙያዎች ሸክስፒየር ምንአልባት ቢያገኛቸው ኑሮ ብዙም በተውኔቱ ባለፋም ነበር። እነዚህ በአዲስ አበባ የሚገኙ ገንዘብ አበዳሪዎችና ስለትክክለኛነቱ አረጋጋጭዎች ሁኔታ ሲታይና ለሕዝቡ በይፋ የተነገረዉ ታሪክ የሚታመን ከሆነ በወርቅ ግዝው ጊዜ "የዳክዩን ፍልስፍና " ያስታዉሰናል። ይኸዉም "ዳክዩ ከመሰለችህ እንደ ዳክየ መንሳፈፍና እንደዳክየ አሽካካ፤ ዳክየ ትሆናለህ" በተመሳሳይ አነጋገር እንደወርቅ ከተብለጨለጨ ብሎም የወርቅ ቅርጽ ካለው እና "ወርቅ" የሚል ከታተመበት በእርግጠኝነት ካለምንም ጥያቄ ወርቅ ነው።

በዳክየ ቲዩር(በዳክየ ጽንሰ ሀሳብ) ላይ ያለው ችግር የውሸት ወርቅ ሆን ብሎ በተቀነባበረ ሁኔታ በኢትዮጵያ ባንክ መገኘቱ የአሳን ረጅምነት የተመለከተውን የተረት ተረት ትረካ ላይ አሳው በማፈንፈን ማግኘት ያለበትን ነገር ሳያገኝ እንደቀረ ሁሉ የባንኩ ደህንነት ጠባቂዎችም የተሰጣቸውን ተግባር ለመወጣት አለመቻላቸው ጋር ይመሳሰላል። በቲዮ ግሬዬ ታዋቂው ሳይንስ ግኝት በይፋ የተወራው የሐሰት ወርቅ ራሱ ሀሰት ነዉ።

"ችግሩ ማንኛውም ሰው ይህንኑ የሀሰት ወርቅ በእጁ ቢያነሳ ወዲያውኑ የውሸት ወርቅ መሆኑን ካለምንም የምርምር ጥበብ ሊያውቅ መቻሉ ላይ ነው ።ለምን ቢባል ክብደቱ ራሱ በቀላሉ የማወቂያ ዘዴ ነው። ወርቁን ቆፍሮ የሚያወጣው ባለሙያ እንኳን ከጉድጓዱ አውጥቶ በሚጭንበት ወቅት የወርቁ ማፈሻ ሳህን የሚሸከመውን መጠን ያውቀዋል፤ክብደቱ በሚጠብቀው መጠን ካልሆነ መሳሪያው በትክክልና በተገቢው አይሰራም ማለት ነው። እንደሚመስለን ከሆነ ወርቁ ከማከማቻዉ ቦታ ተጠርጎ ወጥቷል። በየቀኑ የውሸት ወርቅ ይዞ የሚገባና የውነቱን ወርቅ ይዞ በሚወጣ ኃይል አለ። ከመጀመሪያው ሲገዙ የውሸት ወርቅ ከሆነ ማንኛዉም ሰው በዚህ ተግባር ላይ የተሰማራ ስለወርቅ ምንም እውቀትና ልምድ የለውም ወይም በማጭበርበር ተግባር ተሳታፊ ነው ያሰኛል።"

የባንክ ባለስልጣናት በማጭበርበር ተግባር በተካኑ ባለሙያዎች ተታለው ወይንስ የሀሰት ወርቁ ታሪክ እራሱ ውሸት ነው። ስለሀሰቱ ወርቅ ታሪክ በተመለከተ አያሌ ትንተናዎችና ቲወሪወች የእውነተኛው ወርቅ ሁኔታ ምን እንደደረሰ በየቦታዉ መወያያ ርእስ ሆኗል። አንዳንዶች አስተያየታቸውን ሲሰጡ እዉነተኛዉ ወርቅ በአገር ዉስጥ

እንዳልደረሰ፤ እንዲውም ከመሸጡ ጀምሮ በውጭ ባንኮች እንደታጨቀ ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ አጠቃላይ ሁኔታው በባለስልጣናቱ ምህንድስና በሻንጣ ቀርቃቢዎች አማካኝነት የተፈጸመ ጉዳይ ነዉ ይላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የሀሰት ወርቅ ወደ ደቡብ አፍሪካ የተላከውና ተገኘ የተባለው ባለማወቅም ወይም ሆነ ተብሎ የኢትዮጵያ ባንክ ባለስጣናችን የስራ ትጋት ለማሳየትና ድርጊቱ በወንጀለኞች የተፈፀመ የማስፈጸም የወርቅ ቅብ ብረት ማግኘታቸዉን በማሳወቅ የስራቸውን ዋጋ ከፍ ለማድረግ የተፈጸመ የመሸፈኛ ታሪክ ነው የሚሉ አሉ።

ለሕዝቡ በተገለጸው ይህንኑ ድርጊት የፈፀሙት ወንጀለኞች ሁሉ መታሰራቸውንና ጉዳዩ በምርመራ ላይ እንዳለ ተነግሯል። የወርቅ ነጋዴዎች ገዠዎችና የወርቅ ጥራት ፈታሾች (አጣሪች) በመጨረሻም ስለትክክለኛነቱ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አዳዮች ምን አልባት ሁኔታውን አመቻችተው ለማላከኪያ የተጠቀሙበት ሊሆን ይችላል። የሰጡትም መግለጫ ባንኮችን የዘረፉ ሰዎች ፀሐይ ሳትወጣ ከተማውን ለቀዉ እንደወጡ ገልፀዋል። የተነገረው ይፋ መግለጫ ወይም ታሪክ ሁለት የማያሳምኑ ምክንያቶች አሉት። አንደኛ ይህንን በይፋ የተገለጸ ሁኔታ ለማመን ወርቁ ሲገዛ እውነተኛ ያለመሆኑ መቀበልና መገመት ይኖርበታል እንዲሁም በአንዳንድ የባንክ ባለስልጣናትና ጀሌወቻቸው ቅንብር ባንኩ ረዳት ያጣና የማጭበርበሪያ ሁኔታ ሊካሄድበት ችሏል። ሁለተኛ ምክንያት ወርቅ በተገዛበት ወቅት ትክክለኛ(እዉነተኛ) ሆኖ እያለ የተደራጁ ሌቦች፤እምነት ያጎደሉ ሰራተኞችና ፤ዘራፊዎች በባንኩ ዉስጥ ሳይጠረጠሩ ወይም ሳይታወቁ ሰርገው በመግባት እዉነተኛዉን ወርቅ ወደ ወርቅ ቅብ ብረት ቀይረዉታል በማለት መገመት ይችላል።

ማንኛቸውም ከላይ የተጠቀሱት በይፋ የተወሩ ታሪኮች በቦታው የተፈጸመው ወንጀል ምርመራ፤ ትንተና ጥናት ሊያልፉ አይችሉም። በይፋ የተነገረው የሐሰት ወርቅ ታሪክ ለባንክ መሸጡ ሊታመን የሚያስችለው የተወሰኑ እውነታዎች ሊሟሉ ሲችሉ ነው።

1 የወርቅ ግዡ ጠያቂው ባንክ የመጀመሪያ ወርቅ ሲገዛ፤

2 ባንኩ የአለም አቀፍ የወርቅ ንግድ ላይ ልምድና እዉቀትም ሳይኖረው ሲቀር፤

3. ባንኩ ወርቁን የገዛዉ ከተደራጁ መልካም የስራ ውጤት ካሳዩ የአለም አቀፍ የወርቅ ነጋዴዎች ላይ ሳይሆን በሕገ ወጥ የንግድ ልውውጥ ከሚያደርጉ ላይ ከሆነ፤

4. በወርቅ ግዡ ላይ የተሰማሩት ባለስልጣናት ስለ ወርቅ አነስተኛ ወይም ምንም ስለወርቅ መግዛት እውቀትና ልምድ የሌላቸው ከሆነ፤

5. የባንክ ባለስልጣናት በርካታ ወርቅ ሲገዙ በአለም አቀፍ የወርቅ ግዠ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ አገር ባለሙያዎችን ምክር አልተጠቀሙም፤

6. የባንክ ባለስልጣናት በሚሊዮም ብር የሚያወጣ ወርቅ ገዠን ሁኔታ በትክክል ከወንጀል ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በሚሰጡትም አገልግሎት ታዋቂና መልካም የስራ ባህሪ ያላቸዉና ቴክኒካል አዋቂዎች አልተጠቀመም፤

7. ባንኩ ወርቅ ሲገዛ የጥራት መጠኑን ማረጋገጣ የምስክር ወረቀት በተለመደው የወርቅ ሽያጭ ደንብ ተከትሎ አልፈጸመም ፤

8. የባንክ ባለስልጣናት የወርቅ ነጋዴዎች ነጥረ ሀብቱን መርማሪዎች፤

9. አጽዳቂዎች አንዲሁም ሌሎች እውነተኛ ወርቅ ገዝተዉ ወደ ወርቅ ቅብ በኋላ ለመለወጥ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር በመሃከላቸዉ ለመካፈልም በአገሩ ዉስጥ ቀርተዋል፤ ተንደላቀዉ ለመኖር የሀሰትና የማጭበርበር ስራቸው የማይጋለጥ ተሰውሮ የሚቀር ስለመሰላቸው ።

በተመሳሳይ ሁኔታ የእዉነተኛ ወርቅ ተጠርጎ መወሰዱና በቅብ ብረት መለወጥ ጉዳይ አንዳንድ እዉነታዎች እንዳሉት ያስገምታል፤

1. ባንኩ የወርቅን ምዝገባና ደህንነት ለማስጠበቅ መተዳደሪያ ደንብና ስርአት የለውም፤

2. ባንኩ የወርቁን ጥራት በተከታታይና አልፎ አልፎ የመቆጣጠር ብሎም ባልታሰበና በድንገተኛ ሁኔታ የሚቆጣጠርበት አሰራርና ልማድ የለዉም፤

3. የተደራጁና ልምምድ ያላቸዉ ሌቦች በባንኩ ዉስጥ አሉ የሚያስብለው ያለዉን የደህንነት ጥብቃ በትክክል ስለሚያውቁ የዉነተኛዉን ወርቅ በሀሰት በመለወጥና ወርቁን ጠርጎ ለማውጣት አስችሎአቸዋል፤

4. ይኸዉ በሌብነት የተደረጀ ቡድን ባልታወቀ ጊዜና ወቅት መጠኑ ይኸ ነው ብሎ ለመግለጽ ገና ያልተደረሰበት ጥሬ ገንዘብም ወስዶ ሊሆን ይችላል፤
5. የባንክ ከፍተኛና መካከለኛ ባለስልጣናት፤ ከሌቦችና በማታለሉ ሙያ ከተካኑት ሰዎች ጋር እጅና ጓንት በመሆን በቶን የሚገመተውን ወርቅ በመያዝ በይፋ በቀን ወይም በሽፍንፍን እንዲሰወር ለማድረግ ችለዋል፤

6. የባንክ ከፍተኛ ባለስልጣናት በስራቸዉ ብቃት ማነስ ብቻ ሳይሆን፤ ወንጀለኛ፤ አጥፊወችና ንዝህላኖች ናቸዉ። በአጭሩ በካዝና ውስጥ የተቀመጠ የወርቅ ወደ ዉሸት ወርቅ መለወጥ ማንም ሳያውቀዉ ተደረገ ለማለት አይታመንም። ይልቁንስ ወይም እያዩ እንዳላዩ አልፈውት ካልሆነ በስተቀር በምንም አይነት የማይታመን አይደለም።

በሚሊዩን የሚቆጠር ዶላር የዉሸት ወርቅ መግዣ ከዋለ የባለስልጣናት ችሎታ ማነስ ወይም ለስራቸዉ ብቁ ያለመሆን ምዝበራና እንዝህላልነትን በማሳየቱ የሚያሳዝንን ነዉ። ይህም ለኢትዮጵያ ታላቅ የኢኮኖሚ (የገንዘብ) ውድቀት ነው። በመጀመሪያ ግን የእውነት ወርቅ መኖሩ ወይም ወደ ውሸት ሰው ለውጦት እንደሆነ አናውቅም። በእርግጠኝነት የባንክ ባለስልጣናት ስህተት ይሰራሉ ብለን ቀድመን መናገር ይቸግራል። እኛን የሚመለከቱን በግልጽ የተነገረው የሀሰት ወርቅ የሚያረጋግጠው ቢኖር እኛ የምናውቀውና የምናምንበት ነው። በቀስተ ዳመናው ጫፍ ላይ ወርቅ የያዘ እንስራ የለም ወይም በኢትዮጵያ ባንክ ሙዳይ ውስጥ በእርግጠኝነት የሚያሳስቡን ነገሮች ቢኖሩም ቅሉ ከውሸት ወርቅ ይልቅ ስለ ሐሰተኛ ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ፤የሀሰት ምርጫ፤ የሀሰት ዳኝነት፤ ሀሰተኛ ዴማክራሲ፤ በሀሰተኛ የሰው መብት ገፋፊዎች ጉዳይ ላይ ነው። ትልቅ ዋጋ የምንሰጠዉ ለነፃነት፤ ለዲሞክራሲ የሰው መብትንና ትክክለኛ ዳኝነት በኢትዮጵያ እንዲኖር እና አለም ሁሉ ካለው ወርቅ የበለጠ ወርቃችን እነዚህ መፈክሮቻችን(motto) ናቸው። አይኖቻችንን ዋጋ በምንሰጠዉ ጉዳይ ላይ እናውል።